# ለሳሙኤል ዓለማየሁ

ሀማ ቱማ



12 Jun 1942 - 29 Dec 2005

ቆሞ መሄድ ከብዶ፣ ሰብዕናን ጠብቆ፣
መንበርከኩ ሰፍኖ፣ ከጭቃው ውስጥ ገብቶ፣
የሰው ሰውነቱ ትርጉሙ ሲፈለግ፣
ባሻገር፣ ባሻገር
ከአስመሳይነቱ፣
ከአፋዊው ፋኖ፣
ሆዱን ከሚሞላ፣ ሕዝብና ሀገር ሸጦ፣
ፍርፋሪ ሊገምጥ፣ ከሚዋረድ ቋምጦ፣
የሰው ሰውነቱ፣ ምን ይሆን ምስጢሩ፣
በዓይናችን ስር አለ፣ ሀቀኛው ምላሹ፣
ደብተራውን እዩ!
ሳሙኤልን እዩ!
አበራሽን እዩ!
የኢሕአፓን ልጆች ሁሉን ተመልከቱ።
የሰው ሰውነቱ፣ መጽናናት በእምነቱ፣
ለጭቁን ሕዝብ ላገር፣ ህይወቱን መስጠቱ፣
ደብተራውን እዩ!
ሳሙዔልን አስታውሱ፣
ጀግናውን ኢሕአፓን ሁሌም ተመልከቱ።

(ለሳሙዔል ዓለማየሁ 4ኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ)